# ሊነበብ የሚገባው ታላቅ መጽሐፍ

## ይድረስ ለጎጠኛው መምህር

**ደራሲ ጌታቸው ረዳ**
**ግምገማ በበልጅግ አሊ**

ይድረስ ለጎጠኛው መምህር በጌታቸው ረዳ የተጻፈውን መጽሐፍ ርዕስ ለተመለከተ በመጀመሪያ የሚረዳው ቢኖር ጎጠኛ ለሆነ መምህር የተጻፈ መልዕክት ይሆናል ብሎ ይደመድማል ። ነገር ግን ወደ ውስጥ ገብቶ ለተመለከተውና ላጤነው መጽሐፉ የሚዋጋው፣ የሚያስረዳው አንድ ጎጠኛ መምህርን ብቻ ሳይሆን በአሁኑ ወቅት እየተለመደ የመጣውን ታሪክን ከግል የፖለቲካ አመለካከት አንፃር አጣሞ ማቅረብን ነው ። እውን ነው መጽሐፉ መነሻ ያደረገው " የትግራይ ሕዝብና የትምክህተኞች ሴራ ከትላንት እስከ ዛሬ" በሚል ርዕስ ከመምህር ገብረ ኪዳን ደስታ የተደረሰውን ዘረኛ የሆነ የታሪክ አጻጻፍን ተመርኩዞ ነው ።

አቶ ጌታቸው ረዳ ጎጠኛው ስለ መምህር መጽሐፉ ሲዘረዝሩ ፡ -

> "የትግራይ-ህዝብና-የትምክሕተኞች-ሴራ ከትናንት እስከ ዛሬ በመምህር ገብረኪዳን ደስታ ተደርሶ ለሕትመት በቅቶ ለሕዝብ የተሰራጨው መጽሐፍ አንድን ኢትዮጵያዊ ነገድ ከሌላኛ ኢትዮጵያዊ ነገድ የሚያናንቅ እና የሚያጋጭ ዘረኛ መጽሐፍ በአጼ ዮሐንስና በአጼ ምኒልክ መካከል የነበሩትን የአስተዳደር ጥበብ፣ የስልጣን ፉክክሮችና የዲፕሎማቲክ ስልቶች አጠቃቀም እና ልዩነቶች በማይገባ በወገንተኛነት መልኩ በማቅረብ የአጼ ምኒልክ አስተዳደር "የትግራይን ሕዝብ" ነጥሎ የሚበድል እና ንጉሡ የትግራይን ሕዝብ በዓይነ ቁራኛ በጠላትነት ይመለከቱት እንደነበር አድርጎ የሚያቀርብ፣ እንዲሁም በእሳቸው ምክንያት የትግራይ ሕዝብ ከመልካም የተደላደለ ኑሮና አስተዳደር ወደ ድህነትና "ምኒሊካዊ"(የሸዋ አምሓራ) ጭቆና እንደተሸጋገረ ከማማረሩም በላይ አጼ ምኒልክ የትግራይ-ሕዝብ ጠላት-ብቻ.ሳይሆኑ፣የኢትዮጵያ ጠላት እንደነበሩም ጭምር ባስነዋሪ አቀራረብ መልካም ዝናቸውንና ኩሩ ኢትዮጵያዊነታቸውን ለመግፈፍ የጣረበት መጽሃፍ ነው"።

በመምህር ገብረኪዳን ደስታ የተፃፈውን ዓይነት የታሪክ አጻጻፍ በአሁኑ ወቅት በሰፊው እየተካሄደና ሥር እየሠደደ ያለ ሲሆን በተለይም የወያኔን ዘረኛ የሆነ አመለካከትን የሚደግፉ በሙሉ በሃገራችን ውስጥ የነበረውን ታሪክ ዛሬ እነርሱ ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት በሚያራምዱት የፖለቲካ መሥመር ለማስተካከል የሚያደረጉት ጥረት ውስጥ ጎልቶ ይታያል ።

የአቶ ጌታቸው መጽሐፍ ለወደፊትም የተዛባ ታሪክ ለሚጽፉ ሁሉ የሚያስተላለፈው መልዕክት አለው።መልዕክቱም **እኛም ታሪኩን እናውቀዋለን። ልታዛቡትና ልታበላሹት ለግል ጥቅማችሁ ስትሉ መጭውን ትውልድ ልታወናብዱ አትችሉም** !የሚል ነው ። . . . .ዛሬ የፖለቲካ አመለካከት የተመረኮዘ፣ታሪክን በግል ጥቅም አንጻር መተንተን የተለመደ ተግባር ሆኑዋል ።ዛሬ ለጎጠኝነት ሲባል ታሪክን ማውገርገር ተጀምሯል ። የግል አመለካከትን በማንፀባረቅ አንድን ዘር አውግዞ፣ ኮንኖ መፃፍ ተጀምሯል ። ዛሬ ተጠያቂነት በሌለበት ሁኔታ አንዱን ዘር ከሌላው ጋር ማዋጋት ሥራቸው የሆነ ጸሐፊዎች ተፈጥረዋል ።

ግን የታሪክ ማጣመም ተግባርን በሰፊው የተያያዙት ወያኔዎች ብቻ ሳይሆኑ ከወያኔ ጋር የማንስማማ ነን ባዮች ፣ነገር ግን ከወያኔ የባሰ ዘረኛ የሆኑ ፣ የጎጠኝነት የጠባብ ብሔርተኝነት በሽታ የተጠናወታቸው፣ሌላውን የሚንቁ ፣ ትምክህተኞችም በተለይም በሃገራችን የእርስ በርስ ግጭቶች እንዲስፋፉ የሚፈልጉ ጭምር ናቸው። ለምሳሌ የኦሮሞ ነፃ አውጭ ውስጥ የተሰገሰጉትን ልንመለከት እንችላለን ።

ጌታቸው ረዳ በዚህ መጽሐፋቸው የወያኔ ጸሐፊ መምህር ገብረ ኪዳን ደስታን መጽሐፍ ገጽ በገጽ የተዛባውን ታሪክ እያጋለጡ ፣ ዋቢ ማስረጃዎችን በማቅረብ የወያኔንና የሌሎችንም ጥንፍ የሆነን አመለካከት ነው ሊዋጉ የተነሱት ። አፄ ምንሊክም ሆኑ አፄ ዮሐንስ ለኢትዮጵያ አንድነት ከአበረከቱት አስተዋጽዖ አንፃር በሥልጣን ዘመናቸው የፈፀሚቸው ስህተቶች ሊኖር እንደሚችሉ ልንዘነጋው አይገባም ። ችግሩ የሚነሳው እነዚህ ስህተቶች ከዛሬው የፖለቲካ አመለካከትን አንፃር ወይም ጥቅም አኳያ ልንተነትናቸው ስንሞክር ነው ።

ዛሬ ሃገራችን ከአለችበት ችግር ውስጥ ለመውጣት የሚያስፈልጉን የአቶ ጌታቸው ረዳን ዓይነት ለእውነት የሚቆሙ ፣ሐሰቱን ሐሰት የሚሉ ፣ ከግል ጥቅማቸው ይልቅ የሃገርን ደህንነት የሚያስቀድሙ ፣ የትውልድ አደራን የሚወጡ ታሪክ ፃሐፊዎች ናቸው ።ታሪክ ጸሐፊዎች ከተወለዱበት ዘር ባሻግር የሌላውን ዘር በበጎ ተመልከተው እውነቱን ለሕዝብ ለማቅረብ ጥረት የሚያደርጉ ሊሆኑ ይገባል ።

በዚች አነስተኛ ጽሁፍ አቶ ጌተቻው ረዳ ለኢትዮጵያ አንድነት የሚደርጉትን ትልቅ አስተዋፅዖ ሁሉ ጠቅሼ ማለፋ ይከብደኛል። ግን ተምሳሌነታቸው ከፍተኛ እንደሆነ ልገልፅ እፈልጋለሁ ። በሌላ በኩል ደግሞ መምህር ገብረ ኪዳን ደስታም ይሁን ሌሎች አንዱን ዘር በሌላው ላይ ለማስነሳትና እንደ ሩዋንዳ ዓይነት የዘር በዘር መጨራረስን በመቀስቀሳቸው ታሪክ ለሁሉ ጊዜ ሲወቅሳቸው ይኖራል ።የኛን ዘር ደግፎልናል ብለን ዘረኛ ፀሐፊዎችን የምንከባከብ ከሆነ ከወያኔ ያልተሻልን መሆን ብቻ ሳይሆን የወያኔን እኩይ ዓላማን አራማጆች መሆናችንን ልንገነዘብ ይገባል ። አቶ ጌታቸው ረዳ ከራሳቸው ዘር ባሻግር ቆመው ለሁሉም ኢትዮጵያውያን የሚደርጉትን ጥረት ዓይነት ስናደርግ ነው አንዲቷን ኢትዮጵያን ልንመሰርት የምንችለው ።

በመጨረሻም ይህንን የመሠለ ለሃገር ፣ለትውልድ ጠቃሚ የሆነ መጽሐፍ ለንባብ በማብቃታቸው እንኳን ደስ አልዎት ለማለት እፈልጋለሁ ።ይህ መጽሐፍ ለብዙ ኢትዮጵያውያን በአሁኑ ወቅት ለእውነት ቆመው ከኀጠኝነት፣ አስተሳሰብ ርቀው፣የሚታገሉ እንዳሉ ምስክር ነው ።ይህ መጽሐፍ ኢትዮጵያዊነት እንዲጎለምስ በከፍተኛ ደረጃ አስተዋጽዖ የሚያደርግ ነው ብዬ አምናለሁ ። ኢትዮጵያውያን የሆንና በኢትዮጵያ አንድነት የምናምን ሁሉ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን ፡ብሔረሰቦች በሙሉ ሲጠቁ ወይም አላግባብ ሲወቀሱ አይሆንም ብለን መናገር ስንጀምር ነው ይህ በየቀኑ የምናነሳውና የምንጮኸለት ኢትዮጵያዊነት ሊጠነክር የሚችለው ።

ስለ ኢትዮጵያ የሚያስብ በሰላም ይክረም
በልጅግ አሊ

ይህን ግጥም ከታህሳስ 1999 ፍካት ናፋቂዎች በሚል መጽሐፍ በአቶ በድሉ ዋቅጅራ ለልጃችን ኬርአለም የጻፉትን ነው ። ግጥሙ አቶ ጌታቸው ረዳ ከተነሱበት ዓለማ ጋር በቀጥታ ሊያያዝ ስለሚችል ለአንባቢያን አቀርበዋለሁ።

# *ሀገር ማለት የኔ ልጅ*

*ሀገር ማለት ልጄ፣ ሀገር ማለት፣*
*እንዳይመስልሽ የተወለድሽበት ቦታ ፣ የተወለድሽበት አፈር*
*እትብትሽ የተቀበረበት ፣ ቀድመሽ የተነፈሽው አየር፣*
*ብቻ እንዳይመስልሽ።*
*ሀገር ረቂቅ ነው ቃሉ*
*አገር ውስብስብ ነው ውሉ።*
*ሀገር ማለት ልጄ ፣*
*ሀገር ማለት ምስል ነው ፣በህሊና የምታኖሪው ፣*
*ከማማ መህጸን ከወጣሽበት ቀን ጀምሮ ፤*
*በጠባሽው ጡት ጡጦ ፣*
*በዳህሽበት ደጃፍ በወደቅሽበት ፋፋ*
*በተማርሽበት ትምህርት ቤት፣*
*በተሻገርሽው ዠረት ፣*
*በተሳልሽበት ታቦት ፣ወይ በተማፀንሽው ከራማ ፣*
*በእውነትሽ በስሜትሽ ፣*
*የምትቀበይው ምስል ነው ፣ በህሊናሽ የምታኖሪው ፣*
*ስትወጅ ሰንደቅ ታደርጊው ፣*
*ቢያስጠላሽ የማትቀይሪው።*
*ሀገር ማለት የኔ ልጅ ፣*
*ሀገር ማለት ቋንቋ ነው በአንደበት አይናገሩት፣*
*በጆሮ አያዳምጡት ፣*
*አማርኛ ፣ኦሮሞኛ ፣ቅማንተኛ፣*
*ጉራግኛ ወይ ትግሪኛ ብለው የማይፈርጁት ።*

የኔ ልጅ፣

አማራው አፋሩ ኦሮሞው ሲዳማው ፣ጉራጌኛሽ ባይሰማ፣
ያለገባው እንዳይመስልሽ ፣ ሀዘን ደስታሽን ያልተጋራ።
የየልቦናችንን ሀቅ ፍንትው አድርጎ እያሳየ ፣
ህዝቦችን ከሰንደቃቸው አስተሳስሮ  ያቆየ፣
ሀገር ቋንቋ ነው ልጄ የሁለንተናሽ መስታወት፣
ሲከፋሽ ትሸሸጊበት ፣ ሲደላሽ ትኳኳይበት ።

የኔ ልጅ ፣

አያት ቅም አያትሽ ፣ሰላም ሲሆን ከወልቂጤ አድማስ ማዶ ሸቅጦ፣
ሲያቀና ወረቱን ፣
ለእኔና ለአንቺ መኖሪያ ሲያቀና ቀዬና ቤቱን ፣
ሀገር ጠላት ሲደፍራት ጦሩን ሰብቆ እየፎከረ፣
ከኦሮሞው ከትግሬው ከአፋሩ ከወላይታው ከሁሉም የጦቢያ ልጆች ፣
አጥንቱን እየማገረ ፣
ሀገር ይሉት መግባቢያ ፣ሰንደቅ ይሉት መለያ ፣ሲያቆይልሽ ፣
በጉራግኛ የማትገልጭው በጎጥ የማትገድቢው፣ ስንት አለ ታሪክ መስለሽ።

እና የእኔ ልጅ፣

ለዚህ ነው ሀገር ይሉት ቋንቋ ላንቺ የሚያስፈልግሽ፣
ከወልቂጤ አድማስ ማዶ፤ ለተሳሰረ ታሪክሽ፣
ከወልቂጤ አድማስ ማዶ ፣ለተወጠነው እድገትሽ።
እና ልብ በይ ልጄ ! ሀገር ማለት ቋንቋ ነው ባንደበት አይናገሩት ፣
በጆሮ አያዳምጡት።

ከሁሉም በላይ ልጄ ፣

ተፈጥሮ ከቸረው በረከት ፣የላቡን ፍሬ የሚበላ፣
ሀገር ማለት ወገን ነው ፣ የእኔ የምትይው ከለላ።
ትመኪበት ጥሪት ትደምቂበት ብርሃንሽ፣
የስብዕናሽ ግማሽ ውል ፣ወገን ነው ማህተምሽ፣
ዜጋው ነው ልጄ ሀገርሽ።

መሬትማ የእኔ ልጅ፣

በእምነትሽ ፣እውቀትሽ፣ከልለሽ ካላበጀሽው፣
ለእድገትሽ ውጥን ካልሆነ ፣ለተስፋሽ ካልተመገብሽው፣
መሬትማ ባዳ ነው ላለማው የሚለማ፣
ለተስማማው የሚስማማ።
ዥረቱም ግድ የለውም ፣ቦይ ለማሰለት ይፈሳል፣
ተራራው ደንቆሮ ነው ፣ለቦረቦረው ይበሳል።
መሬቱ አደለም የኔ ልጅ እድርተኛው ነው ሃገርሽ፣
ስትቸገሪ ታድጎ ፣ስትታመሚ አስታሞ፣ ስትሞቺ አፈር የሚያለብስሽ።
በእጅሽ ያለ ብሩህ ጽጌ ፣ሰው ነው ልጄ ሀገርሽ።
ወገን ነው ልጄ ሀገርሽ።

እና የእኔ ልጅ ፣
ሀገር ረቂቅ ነው ቃሉ፣
ሀገር ውስብስብ ነው ውሉ።